- አውራው በግ በይስሐቅ ምትክ ሞተ።
- አውራው በግ የይስሐቅ ምትክ ነበር።

- አብርሃም እግዚአብሔር አውራውን በግ ያዘጋጀበትን ቦታ ምን ብሎ ጠራው?

ዘፍጥረት 22፥14-19

14- ከዚህም የተነሣ፣ አብርሃም የዚያን ስፍራ ስም፣ «እግዚአብሔር ያዘጋጃል» ብሎ ጠራው። እስከ ዛሬ ድረስ፣ «በእግዚአብሔር ተራራ ላይ ይዘጋጃል» ተብሎ ይነገራል።

15- የእግዚአብሔርም መልአክ አብርሃምን ከሰማይ ዳግመኛ ጠራው፤

16- እንዲህም አለው፤ «እግዚአብሔርም በራሴ ማልሁ አለ፤ አንዱን ልጅህን ለእኔ ለመስጠት አልሳሳህምና፣

17- በእርግጥ እባርክሃለሁ፣ ዘርህን እንደ ሰማይ ከዋክብት፣ እንደ ባሕር ዳር አሸዋም አበዛዋለሁ። ዘሮችህም የጠላቶቻቸውን ደጆች ይወርሳሉ፤

18- ቃሌን ስለ ሰማህ የምድር ሕዝቦች ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ።»

19- ከዚያም አብርሃም ወደ አገልጋዮቹ ተመለሰ፤ ተያይዘውም ወደ ቤርሳቤህ ሄዱ፤ አብርሃምም በቤርሳቤህ ኖረ።

- አብርሃም እግዚአብሔር አውራ በግ ያዘጋጀበትን ስፍራ «እግዚአብሔር ያዘጋጃል» ብሎ ጠራው።

- አብርሃም «እግዚአብሔር ያዘጋጃል» ሲል ቦታውን የጠራው ለምንድን ነው?

- አብርሃም እግዚአብሔር አውራውን በግ እንዳዘጋጀ ሁሉ አንድ ቀን ሕዝቡን ለማዳን አዳኝ ያዘጋጃል ብሎ በእግዚአብሔር ስላመነ ነው።



## ትምህርት 22

1. እግዚአብሔር የሰዶምና ገሞራ ሰዎችን ክፋት ያውቅ ነበር?

ሀ- አዎን።

2. ሰዎች እግዚአብሔርን ቢረሱት እርሱ ይረሳቸዋል?

ሀ- አይረሳቸውም።

3. ሰዎች እግዚአብሔርን ቢረሱት እርሱ ኃጢአታቸውን ይረሳል?

ሀ- አይረሳም።

4. እግዚአብሔር ሁሉንም ኃጢአት የሚቀጣው ለምንድን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ፍጹም ስለ ሆነ።

ለ- እግዚአብሔር ሰዎችን ፍጹም አድርጎ ስለ ፈጠራቸው።

ሐ- ሁሉም ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ስለ ሆነ።

5. እግዚአብሔር የሰዶምና የገሞራን ሰዎች ስለ ኃጢአታቸው ወዲያውኑ ያልቀጣቸው ለምን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር ከኃጢአታቸው ንስሐ እንዲገቡ ስለ ፈለገ።

ለ- እግዚአብሔር ሊያድናቸው ስለ ፈለገ።

6. እግዚአብሔር ዛሬ ሰዎችን ስለኃጢአታቸው ወዲያውኑ የማይቀጣቸው ለምንድን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ንስሐ እንዲገቡ ስለሚፈልግ።

ለ- እግዚአብሔር ሊያድናቸው ስለሚፈልግ።

7. እግዚአብሔር ሰዎችን ማስፈራራት ብቻ እንጂ ስለኃጢአታቸው አቀጣቸውም?

ሀ- ይቀጣቸዋል።

ለ- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ ይቀጣል።

8. እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን የሚቀጣበት ጊዜ ሲደርስ እንዳይቀጣ ማድረግ የሚችል አለ?

ሀ- የለም።

9. ኃጢአት ሎጥን ወደ ሰዶም እንደሳበው ሁሉ ኃጢአት በሰዎች ሁሉ ላይ ምን ያደርጋል?

ሀ- ኃጢአት ሰዎችን ወደ ክፋት እየቀረቡ እየቀረቡ እንዲሄዱ ይስባል።

10. እኛ የሰዶምና የገሞራን ሰዎች የምንመስለው እንዴት ነው?

ሀ- እኛም ብዙ ውሸት እንናገራለን።

ለ- እኛም ሌሎችን በሐሰት እንከስሳለን።

ሐ- እኛም ጎረቤቶቻችንን እንረግማለን።

መ- እኛም የሌሎችን ንብረት እንሰርቃለን።

ሠ- እኛም ከሌሎች ሰዎች ሚስቶች ጋር እንተኛለን።

ረ- እኛም ሌሎችን እንገድላለን።

11. እግዚአብሔር ሎጥን ለምን አዳነው?

ሀ- ሎጥ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራቱን ስላወቀ።

ለ- ሎጥ ኃጢአቱ የዘላለም ሞት እንደሚያስከትልበት ስላወቀ።

ሐ- ሎጥ እግዚአብሔር ብቻ ሊያድነው እንደሚችል ስላወቀ።

መ- ሎጥ እግዚአብሔር እርሱን ለማዳን አዳኝ እንደሚልክ ስላመነ።

12. እግዚአብሔር የሎጥን ሚስት የጨው ዐምድ ያደረጋት ለምንድን ነው?



- መሥዋዕቱን ያዘጋጀው እግዚአብሔር ብቻ ነበር ።

- እግዚአብሔር ያዘጋጀው መሥዋዕት ምን ነበር?

- አንድ አውራ በግ።

- አውራው በግ የት ነበር?

- በቀንዶቹ ተይዞ በቁጥቋጦ ውስጥ ነበር።

- አውራው በግ በቁጥቋጦ ውስጥ በቀንዶቹ ሊያዝ እንዴት ቻለ?

- እግዚአብሔር አሥሮት ስለነበር።

- እግዚአብሔር አውራውን በግ በቀንዶቹ ለምን አሠረው?

- እግዚአብሔር በይስሐቅ ምትክ የሚቀበለው ፍጹም የሆነውን መሥዋዕት ብቻ ስለሆነ።

- አውራው በግ በእግሩ ወይም በጭንቅላቱ ታሥሮ ቢሆን ኖሮ ራሱን ለማላቀቅ ሲንፈራገጥ ይጎዳ ነበር።

- እግዚአብሔር ፍጹም ነው።

- እግዚአብሔር የሚቀበለው ፍጹም የሆነውን መሥዋዕት ብቻ ነው።

- አብርሃም ይስሐቅን ከፈታው በኋላ፥ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን አውራ በግ አሥሮ በመሠዊያው ላይ አጋደመው።

- አብርሃም በይስሐቅ ምትክ አውራውን በግ ሠዋው።

- ለአብርሃም የተናገረውና ይስሐቅን ያዳነው ማን ነበር?
- እግዚአብሔር።

- እግዚአብሔር አብርሃም ይስሐቅን እንዳይገድል ጠበቀው።

- ይስሐቅን ያዳነው እግዚአብሔር ብቻ ነው።
- ነገር ግን ሌላ መሥዋዕት ባይኖር ኖሮ ይስሐቅ አይድንም ነበር።

- አብርሃም ሌላ መሥዋዕት ይዞ ነበር?
- አልያዘም።

- ይስሐቅ ሌላ መሥዋዕት ይዞ ነበር?
- አልያዘም።

- እግዚአብሔር ምን አደረገ?

ዘፍጥረት 22፡13

13- አብርሃም ቀና ብሎ ሲመለከት በቁጥቋጦ መካከል ቀንዶቹ የተጠላለፉ አንድ አውራ በግ ከበስተ ኋላው አየ፤ ወደዚያው ሄዶ በጉን አመጣና የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው።

- አብርሃም ሌላ መሥዋዕት አልነበረውም።

- ይስሐቅ ሌላ መሥዋዕት አልነበረውም።
- በይስሐቅ ምትክ የተሰዋውን መሥዋዕት ያዘጋጀው ማን ነበር?
- እግዚአብሔር።



ሀ- የሎጥ ሚስት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመጣስ ወደ ኋላዋ ለተመለከተች።

13. የሎጥ ሚስት ወደ ኋላዋ የተመለከተችው ለምን ነበር?
ሀ- ኃጢአቷን ትወድድ ስለ ነበር ነው።
ለ- ኃጢአቷን መተው ስላልፈለገች ነው።

- እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሣራ ወንድ ልጅ ሊሰጣቸው ቃል ገባ።

- አብርሃም 100 ዓመት ሣራ ደግሞ 90 ዓመት ቢሆናቸውም ምንም ልጅ አልነበራቸውም።

- እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ እንደሚሰጠው የሰጠውን ተስፋ ረስቶ ነበር?

- አልረሳም።

- እግዚአብሔር የገባቸውን ተስፋ ፈጽሞ አይረሳም።
- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ተስፋውን ይፈጽማል።

- እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ ሰለመስጠት አሳቡን ለውጧል?
- አልለወጠም።

- እግዚአብሔር አሳቡን አይለውጥም።
- እግዚአብሔር አደርጋለሁ ያለውን ሁልጊዜ ያደርጋል።

- አብርሃም 100 ዓመት ሣራም 90 ዓመት የሆናት መካን ነበረች።

- ለአብርሃምና ለሣራ ልጅ መስጠት ለእግዚአብሔር አስቸጋሪ ነገር ነውን?
- አይደለም።

- ለእግዚአብሔር ምንም አስቸጋሪ ነገር የለም።

- እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር ማድረግ ይችላል።

- እግዚአብሔር ቃል በገባው መሠረት ለአብርሃምና ለሣራ ወንድ ልጅ ሰጣቸው።

ዘፍጥረት 21፡1-3

1- እግዚአብሔር በተናገረው መሠረት ሣራን አሰባት፤ የገባውን የተስፋ ቃል ፈጸመላት፤

2- ሣራ ፀነሰች፤ ልክ እግዚአብሔር ባለው ጊዜ ለአብርሃም ወንድ ልጅ ወለደችለት።

3- አብርሃም ሣራ የወለደችለትን ልጅ ስሙን ይስሐቅ አለው።

- የ100 ዓመቱ ሰው አብርሃምና 90 ዓመት የሆናት መካን ሴት ሣራ ወንድ ልጅ ማግኘት እንዴት ቻሉ?

- ሕይወትን የሚሰጥ እግዚአብሔር በመሆኑ ነው።
- እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር ማድረግ ስለሚችል ነው።

- እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሣራ የሰጣቸው ልጅ ስም ማን ይባላል?
- ይስሐቅ።

- ከብዙ ዓመታት በኋላ ይስሐቅ አድጎ ጠንካራ ወጣት ሆነ።
- አብርሃምና ሣራ ይስሐቅን በጣም ይወድዱት ነበር።

- አብርሃም እግዚአብሔር ከይስሐቅ ዘር አዳኝ ለማምጣት ማቀዱን ያውቅ ነበር?
- አዎን።



- ይስሐቅን ማዳን የሚችለው ማን ብቻ ነበር?
- እግዚአብሔር።

- ሌሎች ሰዎች እኛን ማዳን ይችላሉ?
- አይችሉም።

- እኛስ ራሳችንን ማዳን እንችላለን?
- አንችልም።

- እኛን ማዳን የሚችለው ማን ነው?
- እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- ኖኅና ቤተሰቡን ያዳነው እግዚአብሔር ብቻ ነበር።
- ሎጥንና ሁለቱን ሴት ልጆቹን ያዳነው እግዚአብሔር ብቻ ነበር።

- ሰዎችን ሁሉ ማዳን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።
- ይስሐቅን ማዳን የሚቻለው ለእግዚአብሔር ብቻ ነበር።

- እግዚአብሔር ይስሐቅን አዳነው?

ዘፍጥረት 22፡11-12

11- የእግዚአብሔር መልአክ ግን ከሰማይ፣ «አብርሃም፤ አብርሃም» ብሎ ጠራው፤ አብርሃምም «እነሆ፤ አለሁ» አለ።

12- እርሱም፣ «እጅህን በብላቴናው ላይ አታሳርፍ፤ ምንም ጉዳት አታድርስበት፤ እነሆ፤ እግዚአብሔርን እንደምትፈራ ተረድቻለሁ፤ ልጅህን ያውም አንዱን ልጅህን ለእኔ ለመስጠት አልሳሳህምና።» አለው።

- አብርሃም ምን አደረገ?
- ይስሐቅን አሥሮ በመሠዊያው ላይ አጋደመው።

- አብርሃም ይስሐቅን ማዳን ችሎ ነበር?
- አልቻለም።

- አብርሃም ይስሐቅን ማዳን ያልቻለው እንዴት ነው?
- አብርሃም ይስሐቅን ለመሠዋት ቢላዋውን አንሥቶ ስለነበር ነው።

- ይስሐቅስ ራሱን ማዳን ችሎ ነበር?
- አልቻለም።

- ይስሐቅ ራሱን ማዳን ያልቻለው እንዴት ነው?
- አብርሃም እጆቹንና እግሮቹን አሥሮት ስለነበር።

- ይስሐቅ ምንም ማምለጫ አልነበረውም።

- ከመርከቡ ውጭ የነበሩት ሰዎች፥ እግዚአብሔር የጥፋት ውኃ በላከባቸው ጊዜ ማምለጥ አልቻሉም።

- የሰዶምና የገሞራ ሰዎች እግዚአብሔር ከሰማይ እሳት በላከባቸው ጊዜ ማምለጥ አልቻሉም።

- የሎጥ ሚስት ወደ ኋላ፥ ወደ ሰዶም ከተማ በተመለከተች ጊዜ ማምለጥ አልቻለችም።

- ማንም ማምለጥ አይችልም።



- አብርሃም እግዚአብሔር ከይስሐቅ ዘር አዳኝ ለማምጣት የገባውን ቃል አስታውሰ።

- አንድ ቀን እግዚአብሔር ለአብርሃም ይስሐቅን የሚመለከት ነገር ተናገረው።

ዘፍጥረት 22፡1-2

1- ከዚህ ሁሉ በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፤ «አብርሃም!» አለው። እርሱም «አቤቱ! አለሁ» አለ።
2- እግዚአብሔርም «የምትወደውን አንዱን ልጅህን፣ ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያ ምድር ሂድ፤ እኔ በማመለክትህ በአንዱ ተራራ ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው» አለው።

- እግዚአብሔር አብርሃም ይስሐቅን እንዲሠዋለት ለምን አዘዘው?

- እግዚአብሔር አብርሃምን ሊፈትነው ስልፈለገ ነው።
- እግዚአብሔር አብርሃምን ሊፈትነው ለምን ፈለገ?

- እግዚአብሔር አብርሃም እርሱን ከይስሐቅ ይልቅ ይወደው እንደ ሆነ ለማወቅ ስለፈለገ ነው።

- እግዚአብሔር አብርሃም ይስሐቅን እንዲሠዋለት ማዘዝ የቻለው እንዴት ነው?

- ለአብርሃም ሕይወት የሰጠው እግዚአብሔር ስለሆነ።

- ለይስሐቅ ሕይወት የሰጠው እግዚአብሔር ስለሆነ።
- የሁሉም ሰዎች ጌታ እግዚአብሔር ስለሆነ።

- ጎረቤታችሁ ሚስታችሁን ማዘዝ ይችላል?
- አይችልም።

- ለምን አይችልም?
- ምክንያቱም ጎረቤታችሁ በሚስታችሁ ላይ ባለመብት ስላልሆነ ነው።

- ጎረቤታችሁ በእርሻ ማሳችሁ ላይ ምን መዝራት እንዳለባችሁ መወሰን ይችላል?

- አይችልም።

- ለምን አይችልም?
- ምክንያቱም ጎረቤታችሁ በማሳችሁ ላይ ባለመብት ስላልሆነ ነው።

- የአብርሃም ጌታ ማን ነው?
- እግዚአብሔር።

- የሰዎች ሁሉ ጌታ ማን ነው?
- እግዚአብሔር።

- እግዚአብሔር የሰዎች ሁሉ ጌታ ስለሆነ የሚፈልገውን ሁሉ ሰዎች እንዲያደርጉለት ማዘዝ ይችላል።

- እግዚአብሔር አብርሃም ይስሐቅን እንዲሠዋ ባዘዘው ጊዜ አብርሃም ምን አደረገ?

ዘፍጥረት 22፡3



- ታዲያ በሽተኛው ከሕመሙ ይድናል?
- አይድንም።

- የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ብቻ አያድናችሁም።
- እንደ አብርሃም የእግዚአብሔርን ቃል ማመን አለባችሁ።

- የእግዚአብሔርን ቃል ሰምታችሁ የማታምኑ ከሆነ ሰይጣንን ትመስላላችሁ።

- የእግዚአብሔርን ቃል ሰምታችሁ የማታምኑበት ከሆነ እግዚአብሔርን ውሸታም እያላችሁት ነው።

- እግዚአብሔር የሚያድነው በእርሱ የሚያምኑትን ብቻ ነው።
- እግዚአብሔር የሚያድነው በቃሉ የሚያምኑትን ብቻ ነው።

- የእግዚአብሔር ቃል የት ነው የሚገኘው?
- በእግዚአብሔር መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው።

- አብርሃምና ይስሐቅ እግዚአብሔር ወዳሳያቸው ቦታ እንደ ደረሱ ምን ተፈጸመ?

ዘፍጥረት 22፡9-10

9- እግዚአብሔር ወዳመለከተው ቦታ እንደ ደረሱ፣ አብርሃም መሠዊያ ሠራ፤ በላዩም ላይ እንጨት ረበረበ፤ ልጁን ይስሐቅንም አሥሮ በመሠዊያው እንጨት ላይ አጋደመው።

10- ከዚያም ልጁን ለማረድ እጁን ዘርግቶ ቢላውን አነሣ።

8- አብርሃም «ልጄ ሆይ፤ ለሚቃጠለው መሥዋዕት የሚሆነውን በግ እግዚአብሔር ራሱ ያዘጋጃል» አለው። ሁለቱም አብረው ጉዞአቸውን ቀጠሉ።

- የአብርሃም መልስ ምን ነበር?
- አብርሃም «እግዚአብሔር ራሱ በጉን ያዘጋጃል» አለ።

- አብርሃም እግዚአብሔር መሥዋዕቱን እንደሚያዘጋጅ አመነ።

- በእግዚአብሔር ማመን በሕይወታችን ከምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ እጅግ አስፈላጊው ነው።

- የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ብቻ አያድነንም።
- ለመዳን የእግዚአብሔርን ቃል ማመን አለብን።

- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡-

- አንድ በጣም የታመመ ሰው ወደ ዶክተር ሄደ።
- ዶክተሩ በሽተኛውን አይቶ ሕመሙ ምን እንደሆነ ነገረው።

- ከዚያም ዶክተሩ በሽተኛው ከሕመሙ ለመዳን እንዲችል የሚያስፈልገውን መድኃኒት ሰጠው።

- በሽተኛው መድኃኒቱን ወሰደና ኪሱ ውስጥ አስቀምጦ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

- ነገር ግን በሽተኛው የታዘዘለትን መድኃኒት ፈጽሞ አልዋጠም።

- በሽተኛው ሐኪሙ ያለውን ሰምቷል።
- መድኃኒቱን ግን አልዋጠም።



3- በማግሥቱ ጠዋት አብርሃም ማልዶ ተነሣ፤ አህያውን ጭኖ፣ ሁለት አገልጋዮቹንና ልጁን ይስሐቅን ይዞ ለመሥዋዕት የሚበቃውን እንጨት ከቆረጠ በኋላ እግዚአብሔር ወዳመለከተው ቦታ ለመሄድ ጉዞውን ጀመረ።

- አብርሃም ለመሠዊያ የሚሆን እንጨት ቆረጠ። ይስሐቅንና ሁለት አገልጋዮቹን አስከትሎ እግዚአብሔር ወደሚያሳየው ቦታ ሄደ።

- አብርሃም ይስሐቅን የሚሰዋው እንዴት ነው?

- አብርሃም ይስሐቅን ከሠዋው እግዚአብሔር ኪዳኑን የሚጠብቀው እንዴት ነው?

- አብርሃም ይስሐቅን ከሠዋው እግዚአብሔር ለአብርሃም ብዙ ልጆችን ሊሰጠው የሚችለው እንዴት አድርጎ ነው?

- አብርሃም ይስሐቅን ከሠዋው እግዚአብሔር አዳኝ ከአብርሃም ዘር መላክ የሚችለው እንዴት ነው?

- እግዚአብሔር ለአብርሃም ይስሐቅ የብዙዎች አባት እንደሚሆንና ከዘሩም አዳኝ እንደሚመጣ ቃል ገብቶለታል።

- እግዚአብሔር አሳቡን ለወጠ?
- አልለወጠም።

- እግዚአብሔር ቃሉን ለማጠፍ ወስኖአል?
- አልወሰነም።
- አብርሃም እግዚአብሔር አሳቡን ይለውጣል ብሎ አስቦ ነበር?

- አላሰበም።

- አብርሃም በእግዚአብሔርና በተስፋው ቃሉ አመነ።

- አብርሃም እግዚአብሔር የገባውን ቃል እንደሚጠብቅ አመነ።

- አብርሃም እግዚአብሔር ብዙ ዘሮችን እንደሚሰጠው የገባለትን ቃል ኪዳን አመነ።

- አብርሃም እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ የገባውን ቃል አመነ።

- አብርሃም ልጁ ይስሐቅን ከሠዋ እግዚአብሔር ምን ያደርጋል ብሎ አመነ?

- ይስሐቅን ከሠዋ እግዚአብሔር ከሞት ያስነሣዋል ብሎ አመነ።

- የአብርሃም እምነት ከአዳምና ከሔዋን እምነት የተለየ ነበር።

- እግዚአብሔር በኤድን የአትክልት ስፍራ ለአዳምና ለሔዋን፥ መልካምና ክፉን ከሚታስታውቀው ዛፍ ከበሉ እንደሚሞቱ ነገራቸው።

- አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር አላመኑም።

- አብርሃም ግን በእግዚአብሔር አመነ።

- አብርሃም በእግዚአብሔር ስላመነ ይስሐቅንና ሁለቱን አገልጋዮቹን እግዚአብሔር ወደሚያሳየው ቦታ ወሰዳቸው።

ዘፍጥረት 22፡4-6

4- በሦስተኛው ቀን አብርሃም ቀና ብሎ ቦታውን ከሩቅ ተመለከተ።
5- አገልጋዮቹንም፣ «እናንተ አህያውን ይዛችሁ እዚህ ቆዩን፤ እኔና ልጄ ግን ወደዚያ ሄደን ለእግዚአብሔር ሰግደን እንመላለሳለን» አላቸው።



6- አብርሃም ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆነውን እንጨት ወስዶ፣ ልጁን ይስሐቅን አሸከመው፤ እሳቱንና ቢለዋውንም ራሱ ያዘ። ሁለቱም አብረው ሄዱ።

- አብርሃምና ይስሐቅ አብረው በመጓዝ ላይ ሳሉ ይስሐቅ አባቱን አንድ ነገር ጠየቀው።

ዘፍጥረት 22፡6-7

6- ሁለቱም አብረው ሄዱ።
7- ይስሐቅም አባቱን አብርሃምን፣ «አባቴ ሆይ፣ አለው። አብርሃምም፣ «እነሆኝ፤ አለሁ ልጄ» አለው። ይስሐቅም፣ «እሳቱና እንጨቱ ይኸው፤ ነገር ግን የሚቃጠለው መሥዋዕት የት አለ?» ብሎ ጠየቀው።

- የይስሐቅ ጥያቄ ምን ነበር?

- «የመሥዋዕቱ በግ የት አለ?» የሚል ነበር።

- ይስሐቅ አባቱ አብርሃም መሥዋዕት እንደሚያቀርብ አውቋል።

- ይስሐቅ እሳቱንና እንጨቱን ይዘው በመሄድ ላይ መሆናቸውን ያውቃል።

- ይሁን እንጂ በግ ይዘው ያልሄዱበትን ምክንያት አላወቀም።

- አብርሃም ለይስሐቅ የሰጠው መልስ ምን ነበር?

ዘፍጥረት 22፡8